የጤና ሚኒስቴር፣ ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH, ETHIOPIA

የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት
Ethiopian Public Health Institute

# የኮሮና ቫይረስ በሽታ ምላሽ አሰጣጥን (የኮቪድ-19) አስመልክቶ የተዘጋጀ መግለጫ

ባለፉት 24 ሰዓት ውስጥ በተደረገው የ1073 ላቦራቶሪ ምርመራ ሁለት (2) ሰዎች በኮሮና ቫይረስ መያዛቸው ተረጋግጧል። በአጠቃላይ በሀገራችን በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች ቁጥር አንድ መቶ አስራ ስድስት (116) ደርሷል። በሌላ መልኩ በትላንትናው ዕለት አምስት (5) ሰዎች (4 ከአዲስ አበባና 1ከድሬዳዋ) ከበሽታው ያገገሙ ሲሆን በአጠቃላይ በሀገራችን ከበሽታው ያገገሙ ሰዎች ቁጥር ሃያ አንድ (21) ነው። በዛሬው ዕለት በቫይረሱ የተያዙ ታማሚዎች ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፣

| ተ.ቁ | ዜግነት | መኖሪያ ቦታ | እድሜ | ፆታ | የውጭ ሀገር ጉዞ ታሪክ | በበሽታው ከተያዘ ሰው ጋር ግንኙነት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ኢትዮጵያዊ | በአፋር ክልል ገዋኔ | 22 | ወንድ | የለውም | በመጣራት ላይ ያለ |
| 2 | አሜሪካዊ (ትውለደ ኢትዮጵያዊ) | | 54 | ወንድ | ከአሜሪካ የመጣና በለይቶ ማቆያ ውስጥ ያለ | የለውም |

## በሀገራችን የኮሮና ቫይረስ የሁኔታ መግለጫ

| | |
|---|---|
| አጠቃላይ የተከናወነ የላብራቶሪ ምርመራ | 9771 |
| በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ የተከናወነ የላብራቶሪ ምርመራ | 1073 |
| በዛሬው ዕለት በበሽታ መያዛቸው በላብራቶሪ የተረጋገጠ | 2 |
| በአጠቃላይ በቫይረሱ ተይዘው በለይቶ ከህክምና ውስጥ ያሉ | 90 |
| በፅኑ ህክምና ላይ ያሉ | 0 |
| አዲስ ያገገሙ | 5 |
| በአጠቃላይ ያገገሙ | 21 |
| በበሽታው ሕይወታቸው ያለፈ | 3 |
| ወደ ሀገራቸው የተመለሱ | 2 |
| እስከ አሁን ድረስ በበሽታው የተያዙ ሰዎች ቁጥር | 116 |

ህብረተሰቡ የበሽታውን ስርጭት ግምት ውስጥ በማስገባት፡

- በቫይረሱ መያዛቸው ከተረጋገጡ ሰዎች ጋር የቅርብ ንክኪ ያላቸው ግለሰቦች በአፋጣኝ በ8335 ወይም 952 በመደወል ወይም ባሉበት ክልል በተዘጋጁ ነፃ የስልክ መስመሮች በመደወል ሪፖርት እንዲያደርጉ ወይም በአካባቢው ለሚገኙ ጤና ተቋማት እንዲያሳውቁ፣
- ለተለያዩ ጉዳዮች በአንድ ቦታ መሰባሰብ በማስወገድ፣ እጅን አዘውትሮ በመታጠብ፣ በአካል ንክኪ የሚደረግ ሰላምታን በመተውና አካላዊ መራራቅን ተግባራዊ በማድረግ የበሽታውን ስርጭት እንዲከላከል እናሳስባለን።

በማንኛውም ሰዓት ጥቆማ ለመስጠትና መረጃ ለማግኘት በነፃ የስልክ መስመር 8335 ወይም በ952 ወይም በመደበኛ የስልክ ቁጥር 0118276796 በመደወል ወይም በኢሜል አድራሻችን ephieoc@gmail.com በመጠቀም ወይም ባሉበት ክልል በተዘጋጁ ነፃ የስልክ መስመሮች በመደወል ሪፖርት እንዲያደርጉ ወይም በአካባቢው ለሚገኙ ጤና ተቋማት በስልክ እንዲያሳውቁ እንጠይቀለን።

ዶ/ር ሊያ ታደሰ
የጤና ሚኒስትር
ሚያዝያ 14 ፣ 2012 ዓ.ም